በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከሜይ 1-31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ

## ግምገማ እንዲሁም

## ከጁን 1-30/2024

## የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁን 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ........- 1 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ........- 3 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........- 4 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት........- 4 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር........- 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ ........- 4 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........- 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ........- 5 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........- 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ........- 6 -

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ........- 7 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከጁን 1-30፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........- 8 -

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........- 8 -

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉ.ሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........- 9 -




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በሜይ የመጀመሪያው አስር ቀናት በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በደቡብ፣ በመካከለኛው፣ በደቡብ ምዕራብ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋንና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋርተያይዞ በብዙ ስፍራዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ ከበድ መጠን ያለው ዝናብ አገኝተዋል፡፡ በሁለተኛው አስር ቀናት ዝናቡ በመጠን ከመጀመሪያው አስር ቀናት በተወሰነ መልኩ የመቀነስ አዝማሚያ ያሳየ ቢሆንም በስርጭት ረገድ በልግ ዋነኛ እና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን የሆኑትን የሀገሪቱ ክፍሎችን የሸፈነ ሲሆን፣ በሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበረው ጠንካራ የደመና ሽፋን ጋር ተያይዞ በብዙ ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች በተለይም ከሜይ የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ጀምሮ በብዙ ስፍራዎቻቸው ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በስርጭት ቀንሶ ተስተውሏል፡፡

በአጠቃላይ በሜይ ወር በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በስርጭት ብዙ ቦታዎችን ያዳረሰ ሲሆን፤ በበርካታ ቦታዎቻቸው ላይም ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል፤ በአርባ ምንጭ 34.9፣ 38.0፣ 62.5 እና 43.4፤ አለም ተፈሪ 52.2፤ በቡሬ 57.7፣ በቢሾፍቱ 41.0፤ በነቀምቱ 67.0 እና 57.6፤ በአርጆ 36.6፤ በነገሌ 45.1፣ 31.9፤ በአዋሽ አርባ 30.0፣ በብላቴ 46.6፤ በቦሬ 39.2 እና 37.2፤ በቡርጂ 39.0፤ በዲላ 36.4 እና 38.2፤ በዶሎመና 30.2፣ 40.1፣ 60.0 እና 30.0 ፤ በገዋኔ 43.3፤ በጋቲራ 64.0 እና 35.8፤ በጋምቤላ 46.7፤ በጊምቢ 37.9፤ በጊዳ አያና 80.0፤50፤ በሊሙ ገነት 43.9፤ በማሻ 30.4፤ በቡሌ ሆራ 32.8 እና 48.0፤ በኮንሶ 38.4 እና 30.0፤ በሞያሌ 85.4፤ በአዳማ 36.1፤ በወላይታ ሶዶ 35.7፤ 32.2 እና 55.0፣ በያበሎ 31.6 እና 36.5፤ በሂርና 36.4 እና 37 በኮምቦልቻ 46.8፤ በጨለንቆ 40.2፣ በዶሎ ኦዶ 96.1፤ ኮምቦልቻ (ምስራቅ ሀረርጌ) 46.8 እና 38.8፤ በቴፒ 35.2 እና 35.4፤ በባቢሌ 44.0፤ በአድዋ 32.0፤ በአልጌ 40.0 እና 40.6፤ በጭፍራ 42.5፤ በስንቃጣ 43.9 እና 32.2፤ በደብረ ማርቆስ 35.8፤ በአቦምሳ 35.0፤ በጂንካ 79.8፤ በላይበር



ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

58.4፤ በማጂ 30.0፤ በወላይታ ሶዶ 99.9 እንዲሁም በኩርፋ ጨሌ 34.0 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

በሜይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር እና ጅማ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ ዞን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከሱማሌ ክልል አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ እና ካማሺ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ሀሪ ዞን፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ ዞን፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ ጠምባሮ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አማሮ፣ ባስኬቶ፣ ቡረጂ፣ ደራሼ፣ ጋሞ፣ ጌደኦ፣ ጎፋ፣ ኮንሶ፣ ደቡብ ኦሞ እና ወለይታ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች እንዲሁም ሀረር ላይ ከ81-322 የሚደርስ ዝናብ ከ11-22 ቀናት ያህል ነበራቸው። በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ጀረር፣ ዶሎ፣ ቆራሄ፣ ኖጎብ እና ሸበሌ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን፣ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን እንዲሁም አዲስ አበባ እና ድሬ ዳዋ ላይ ከ10-80 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-10 ቀናት ያህል ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2) ።


በሜይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ጀረር፣ ኤረር፣ ዶሎ፣ ቆራሄ፣ ኖጎብ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀውሲ፣ ሀሪ እና ገቢ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ ዞን፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ የኢታንግ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ልዩ ዞን፣ ኑዌር እና አኝዋክ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀዲያ፣ሀላባ፣ከምባታ እና ጠምባሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አማሮ፣ ባስኬቶ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ኮንሶ፣ ደቡብ ኦሞ እና ወላይታ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ከፋ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች እንዲሁም ሀረር እና ድሬ ዳዋ ላይ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡


በሌላ በኩል በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፤ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ36.4-43.8 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ፡፡





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሜይ ወር የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎችም ሆነ በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተለያዩ የግብርና ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ ወቅታቸውን ጠብቀው አስቀድመው የተዘሩ የበልግ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት፣ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች እድገታቸው የተሟላ ለማድረግ እና ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም አስቀድመው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራትና ማሳን ለማዘጋጀት አዎንታዊ ጎን ነበረው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ በተለይም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት የግጦሽ ሳርና ለአረንጓዴ እጽዋት ልምላሜ እንዲሁም ለመጠጥ ዉሃ አቅርቦት አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር(ካርታ 5)፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ወር በባሮ አኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ አዋሽ እና አፋር ደናክል እንዲሁም የላይኛው እና የመካከለኛው ተከዜ እና አባይ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ለገጸ ምድርም ሆነ ለከርሰ ምድር የውኃ ሀብት መሻሻል እንዲሁም የግድቦችንና እና የወንዞች የውኃ አቅም ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ

በመደበኛው ሁኔታ ወቅታዊው የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር አብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳርሳል ።

በመጪው የጁን ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ አንጻራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው የአሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም በተለይም በምዕራብ አጋማሽ ኢትዮጵያ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ እንደሚሆን  የሚጠበቅ ሲሆን በአንዳንድ አካባቢዎችም ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ደመናዎች ላይ በመነሳት ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7 )። በአጠቃላይ በጁን ወር ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ጉጂ፤አዲስ አበባ፣ ድሬ ዳዋ እና ሀረር፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ እና ምዕራብ ጎንደር፣ አዊ ዞን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ደቡብ ጎንደር፤ ከትግራይ ክልል  ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል  ኮንሶ፣ አማሮ፣ አሌ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ ባስኬቶ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል  ሀላባ፣ ሃዲያ፣ ጠምባሮ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኝዋክ፣ የኢታንግ ልዩ ዞን እና ኑዌር ዞኖች፣  ከቀላል  እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7) ።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066    ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከጁን 1-30፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የጁን ወር በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው እርጥበት የመኸር አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበትን የሚያሻሽል ከመሆኑ አንፃር በወቅቱ የማሳ ዝግጅት ለማከናወንም ሆነ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም አስቀድመው ተዘርተው በተለያዩ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱ የበልግ ሰብሎች፣ ከኤፕሪል ጀምሮ በነበረው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፣ የጓሮ አትክልቶች እና ቋሚ ተክሎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላም በኩል የሚጠበቀው እርጥበት በደረሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድርግ በመካከል በሚገኙ ደረቅ ቀናት የሰብል ስብሰባ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የጁን ወር የሚጠበቀው እርጥበት በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አፋር ደናክሊ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የገፀ ምድር እና የከርሰ ምድር የውሃ ሀብትን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et